## ዓመታዊ ሪፖርት

ብዙዎቻችሁ እንደምታውቁት ይህ ዌብ ሳይት ከተጀመረ (ጃንዋሪ 1 ቀን 2003) ሦስተኛ□ዓመቱን ይዟል። በተቻለን አቅም የቤተ ክርስቲያናችንን እምነቷ፣ ሥርዓቷ እንዲሁም ታሪኳን በሙሉ እዚህ ዌብ ሳይት ማ
ስፈር ባይቻልም ዋና ዋናውን ክፍል ተከታይ ምእመናኖቿ ማወቅ ያለባቸውን ለማሳወቅ የተቻለንን እየጣር
ን ነው። እንዲሁም ወቅታዊ ትምህርቶችን፣ የዕለተ ሰንበት ምስባክ፣ ወንጌሉንና ትምህርቱን በማውጣት ምእመናን አስቀድመው እንዲማሩ እያደረግን ነው። በሳምንት አንድ ጊዜ ተጨማሪ ትምህርታዊ ጽሑፎች
ን በማውጣት ምእመናን ወቅታዊ በዓላትን ትርጉማቸውን እንዲያውቁ እየሞከርን ነው።

ይህን አገልግሎት መስጠት ከጀመርንበት ጊዜ ማለትም ላለፉት 3 ዓመታት ከዕለት ወደ ዕለት እየጨመረ የመጣውም የጎብኝዎች ቁጥር በአሁኑ ወቅት በወር በአማካኝ ከ1.6 ሚሊዮን በላይ ደርሷል። ከምናገኘው የእስታቲስቲክ መረጃ እንደተረዳነው ከእንግሊዘኛ□ቋንቋ□ቀጥሎ ብዙ ሰው ከጀርመንኛና ፈረንሳይኛ□ተናጋሪ ሀገሮች ስለሚገባ በ2006 ዓመት ሪፖርት ላይ ልንሠራ ከወጠናቸው አንዱ በእነዚህ ቋንቋዎች ማዘጋጀት ነ
በር። እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ሆኖ በዚህ በ2007 መጀመሪያ ላይ ዕቅዳችንን መፈጸም ችለናል። በጀር
መንኛ□ቋንቋ□ትርጉም የተባበሩንን አቶ መረተ ግዛውን ከፍራንክፈርት (ጀርመን) እንዲሁም ዌብ ሳይታቸው ላይ ያለውን የፈረንሳይኛ□ጽሑፎች ኮፒ አድርገን እንድንጠቀም የፈቀዱልንን ሚስተር ማለረን ከፈረንሳይ ከልብ እናመስግናለን። ለጊዜው በአብዛኛው በእነዚህ ቋንቋዎች የቀረቡት ጽሑፎች ከሌላ ዌብ ሳይቶች ጋ
ር በማገናኘት ሲሆን፤ ዓላማችን ግን ሁሉም በውጭ ቋንቋ የተዘጋጁት ጽሑፎች አንድ ዓይነት መልእክት እንዲኖራቸው ነው። ስለዚህ ይህን ዓላማ ከግብ ለማድረስ የእናንተን ትብብር እንጠይቃለን ማለትም ችሎ
ታው ያላችሁ በመተርጎም ወይም ደግሞ ስፖንሰር በመሆን በማስተርጎም ነው። ስለዚህ እምነታችን እንዲስ
ፋፋ የበኩላችሁን ጥረት እንድታደርጉ እናሳስባለን።

ይህ ዌብ ሳይት እንዲያድግ መጻሕፍቶቻቸውን እንድንጠቀም የፈቀዱልንን ብጹእ አቡነ ገብርኤልን፣ ብጹ
እ አቡነ መልከ ጼዴቅን፤ መምህር ብርሃኑ ጎበና እንዲሁም ሌሎች መምህራንን፣ ወቅታዊ የሆኑ ጽሑፎች
ን ምንጭ አድርገን የምንጠቀምበትን የመለከትና ሐመር መጽሔት አዘጋጆችን፤ እንዲሁም ትምህርታዊ ጽ
ሑፎችንና ታይፕ በማስደረግ መዝሙራትን ሌሎችንም በሚያስፈልገን የሚረዳንን በአዲስ አበባ በምስካየ ኅዙናን መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን ሥር የሚገኘውን የተምሮ ማስተማር መንፈሳዊ ማኅበርን፤ እንዲሁ
ም የቤተ ክርሰቲያን ፍቅርና የዚህ ዌብ ሳይት ዓላማው የገባቸው ጊዜያቸውን መስዋዕት አድርገው ብዙው
ን ጽሑፍ ታይፕ በማድረግ ከአውሮፓና ከሰሜን አሜሪካ የተባበሩትን ሁሉ ከልብ እያመሰገንን፤ እግዚአብ
ሔር አምላክ ዋጋቸውን ውለታቸውን እንዲከፍላቸው ከልብ እንጸልያለን።

በቤተ ክርስቲያን በቅዳሴ አገልግሎት ጊዜ በብዙ ቦታዎች ሥርዓተ ጸሎቱ ምዕመናን የሚከታተሉበት መጻ
ህፍት ስላልተዘጋጀ ምዕመናን አብረው ለመከታተል ይቸገራሉ። ይኽንንም በማሰብ የሎሰ አንጀለስ ድንግ
ል ማርያም ቤተ ክርስቲያን ዘወትር እሁድ በቅዳሴ ጊዜ በscreen
ላይ ምዕመናን የቅዳሴ ተሰጥኦ የሚከታተሉበት በሦስት ቋንቋ የተዘጋጀ (ግዕዝ፣ አማርኛና እንግሊዘኛ) በው
ጭው ዓለም ያለችው ቤተ ክርስቲያናችን እንድትጠቀምበት በዚህ ዌብ ሳይት ላይ እንዲወጣ ስለፈቀዱ ከ
ልብ እናመሰግናለን። በዚህ ዌብ ሳይት ላይ የተዘጋጀው በpdf ሲሆን በpower point እንዲላክችሁ
የምትፈልጉ ከሆነ ኢሜይል አድርጉልን። ለጊዜው የተዘጋጀው ቅዳሴ የሐዋርያት፣ የጌታ፣
የዲዮስቆሮስና የእመቤታችን ነው። ወደፊት የተቀሩትን ቅዳሴዎች በዚሁ ዓይነት ለማዘጋጀት ዕቅድ አለ።
በተጨማሪም ዘወትር እሁድ በቤተ ክርስቲያኗ የሚሰበኩትን ትምህርቶችና ስብከቶች ሌሎች ምእመናን ሰምተው መንፈሳዊ ሕይወታቸውን እንዲያጎለምሱ በዚህ ዌብ ሳይት ላይ እንዲወጣ ስለፈቀዱልን በድጋሚ እናመሰግናለን። በተላይ በዚህ ዌብ ሳይት ላይ የብዙዎችን ሕይወት የሚማርክና የሚያንጽ ትምህርት ለሚ
መግቡን፤ በጣም ታዋቂ የሆኑትን ታላቁን መምህር አባ ወ/ትንሣኤንና ቀሲስ መላኩን ከልብ ልናመሰግን እ
ንወዳለን። እግዚአብሔር አምላክ ለእነዚህ ሰባክያን ወንጌል ረጅም ዕድሜን፤ ጤንነትን እንዲሰጥልን በጸ
ሎት አምላካችንን እንለምናለን። ጸሎታችን ለእነዚህ መምህራን ብቻ ሳይሆን ለሌሎችም የእግዚአብሔር መንግሥት ትስፋፋ ዘንድ ደከመን ሰለቸን ሳይሉ በስብከተ ወንጌል ለሚደክሙ ሁሉ ነው። የዚችው ቤተ ክርስቲያን አባል የሆኑት አቶ ዘላለም ባይለየኝም በየጊዜው የየዕለተ ሰንበት ግጻዌና ትምህርትን ታይፕ በ
ማድረግ ላለፉት ዓመታት አስተዋጽኦ በማድረጋቸው ከልብ እናመሰግናለን።

ከቤተ ክርስቲያናች ቅርስና ትምህርቷ አኳያ ይህ ዌብ ሳይት ገና በጣም በጣም ጥቂት የሆነ ትምህርታዊ ጽሑፎችን የያዘ ሲሆን ነገር ግን ብዙ ተጨማሪ ትምህርቶችና መጻሕፍት ወደፊት ለመጨመር እቅድ አለ

**። አሁንም ብዙ የተወጠነ ዕቅድ ስላለ አስተዋጿቸው እንደሚቀጥልና ሌሎችም ለዚህ ቅዱስ ተግባር ለመ
ተባበር የምትፈልጉ ካላችሁ ከአምላካችን ዘንድ በረከት የምትቀበሉበት ስለሆነ በምን ዓይነት መርዳት እ
ንደምትችሉ እንድትጽፉልን አደራ እንላለን። በጣም የምንፈልገው ዕርዳታ ታይፕ በማድረግና በትርጉም
ሥራ ነው።**

**በአለፈው ዓመት ከጠቀስናቸው ዕቅዶች መካከል አብዛኛውን ዓመቱ ከማለቁ በፊት ለመፈጸም ችለናል።
እነርሱም፤**

1) **የቅዱስ ያሬድን የዐበይት በዓላት ዜማዎችን**
2) 14 **ቅዳሴዎችን በዜማም በጽሑፍም** (**በግእዝ፣ አማርኛ፣ እንግሊዘኛ**)
3) **የዕለተ እሑድ አገልግሎትን ማለትም ሰዓታቱን፣ የዕለቱን ቅዳሴ ከነትምህርቱ፣ ሙሉ የሰንበት
   ትምህርት ቤት መርሐ ግብር በየእሁዱ ማቅረብ፣**
4) **ግብረ ዲቁናና መማር ለሚፈልጉ ሙሉ ትምህርቱን እዚህ ዌብ ሳይት ላይ ማቅረብ**
5) **የቤተ ክርስቲያን የአገልግሎት ዜማዎችን እዚህ ዌብ ሳይት ላይ ማቅረብ**
6) **ቀደም ብለው የተቀረጹ ዜማዎችን አርካይቭ ማድረግና ቀድሞ የወጡ መዝሙራት
   ዜማቸው እንዳይረሳ አስቀርጾ ማቅረብ፤**
7) **የብሉይ ኪዳን 2ኛ የቀኖና መጻሕፍትንና ሌሎችንም እዚህ ዌብ ሳይት ላይ ማቅረብ**

**እነዚህ ዕቅዶችን ለመፈጸም ያስቻለን የአንዳንድ ሰዎች ትብብር ስለሆነ እነርሱን በዚህ አጋጣሚ ማመስገ
ን እንፈልጋለን። በመጀመሪያ አባ ቶማስ ከተማ 14ቱን ቅዳሴ ታይፕ በማድረግ (185 ገጽ)፣ ቃላቱን በማረ
ም ለቤተ ክርስቲያናችን ከፍተኛ አስተዋጽኦ በማድረጋቸው ከልብ እንመሰግናለን። እንዲሁም በእንግሊዘኛ
ው ገጽ ላይ በየሳምንቱ የእንግሊዘኛ ስብከት ስለሚያቀርቡልን ከልብ እናመሰግናለን። በተጨማሪም በቅር
ብ ቀን ቅዳሴ በእንግሊዘኛ ተቀርጾ እናንት ምእመናን ትሰሙት ዘንድ እናቀርባለን።**

**በመቀጠልም መሪጌታ ክፍሉ ከሎስ አንጀለስ ድንግል ማርያም በዚህ ዌብ ሳይት ላይ ለተጀመረው የግብረ
ድቁና ትምህርት ምስባኩን በማዜም ሌሎችንም ማስተማሪያ ዜማዎችን በመስራት እየተባበሩን ሲሆን በ
ተጨማሪም ከዚህ በፊት በዚህ በሎስ አንጀለስ የተቀረጹ ማኅሌታዊ ዜማዎች ሌሎች ምዕመናን ይሰሟቸ
ው ዘንድ ስላበረከቱ ከልብ እናመሰግናለን። እዚህ ዌብ ሳይት ላይ የግብረ ዲቁናው ትምህርት የተሟላ ይ
ሆን ዘንድ አባ ላእከ ማርያም ውዳሴ ማርያም በግእዝ እንዴት እንደሚነበብ ጊዜያቸውን ወስደው ስለተቀ
ረጹ እናመሰግናለን።**

**አቶ ወንድወሰን አሰፋ ከእንግሊዝ (ለንደን) ወደ ኢትዮጵያ ለዕረፍት በሄዱበት ወቅት በበዓታ ማርያም ቤ
ተ ክርስቲያን በመገኘት ተሰምቶ የማይጠገበውን ማኅሌተ ያሬድ (የገናና የፋሲካን) ቀርጸው አበርክተዋል
። በተጨማሪም በለንደን ደብረ ጽዮን ቅድስት ማርያም የተቀረጸ የአዲስ ዓመትና የኅዳር ጽዮን ዜማ ስላ
በረከቱልን ከልብ እናመሰግናለን። ሌሎችም ምዕመናን ዜማዎች ወይም ጠቃሚ ጽሑፎች ካላችሁ ብትል
ኩልን ሌሎች ወገኖቻችን ሰምተው የሚጠቀሙበት ይሆናል።**

**ሁላችሁም እንደምታውቁት በአሁኑ ወቅት እጅግ ቁጥራቸው የበዛ መዝሙራት እየወጡ ቢሆንም ነግር ግ
ን መንፈሳዊ ማኅበራት (የሰንበት ት/ቤት) ከተመሠረቱበት ከ**1949 **ዓ.ም ጀምሮ የወጡት መዝሙራት እየተ
ረሱ በመሄዳቸው እነዚህ መዝሙራት ለታሪክ ተቀርጸው እንዲቀሩ ለማድረግና ምዕመናንም ጣዕማቸውን
እንዲያውቁት እንዲለማመዱት በማሰብ በ**1970 **ዓ.ም ከታተመው መዝሙረ ተዋሕዶና መዝሙር ኅሩይ ላ
ይ ያሉትን መዝሙራት ተቀርጸው በተከታታይ እንዲወጡ እያደረግን ነው። በዚህም መሠረት በካሊፎርን
ያ ከሚገኙት የሰንበት ት/ቤቶች አንዱ የሆነው የሃይማኖተ አበው ሰንበት ትምህርት ቤት መዘምራን ባለ
ፈው ግንቦት ወር የመጀመሪያውን ቁጥር -** 1(**ከዐቢይ ጾም እስከ ጰራቅሊጦስ**) **አውጥተዋል። ቁጥር ሁለት
ን** (**ከአዲስ ዓመት እስከ ገና መግቢያ**) **ደግሞ በቅድስት ማርያም የማኅበረ ሰላም ሰንበት ትምህርት ባለፈ
ው ወር ቁጥር - ሁለትን አቅርበዋል። እንዲሁም በአለፈው በሚያዚያ ወር በለንደን የሚገኙ መዘምራን ቁ
ጥር ሶስትን** (**የገና መዝሙራት**) **የተቀረጹ ሲሆን በነሐሴ ወር ለስርጭት እንደሚደርስ ታውቋል። እንዲሁ
ም ቁጥር አራትን በኦክላንድ መድኃኔዓለም የሐመረ ኖኅ ሰንበት ት/ቤት እንደሚያስቀርጹ ታውቋል። ይህ
ንን ታላቅ ታሪካዊ ሥራ ለመስራት የእነዚህ ሰንበት ት/ቤት ወጣቶች በመነሳታቸው ከፍ ያለ ምስጋና እያ
ቀረብን ፤ እግዚአብሔር አምላክ ብርታቱን እንዲሰጣቸው፤ ዓላማቸውም ከግቡ እንዲደርስ በጸሎት እናስ
ባቸዋለን።**

**በመጨረሻም በአለፉት ከ**20 **ዓመታት በላይ ብዙ ቤተ ክርስቲያኖች በውጭው ዓለም እየተቋቋሙ ይገኛሉ ፤ ይሁን እንጂ አብያተ ክርስቲያናቱ የሚተዳደሩት ቀደም ብሎ ቤተ ክርስቲያን በምትተዳደርበት ደንብ** (**ቃለ አዋዲ**) **አይደለም። ደግሞም ቃለ አዋዲው ለውጭው ዓለም እንዲያገለግል ተብሎም የተዘጋጀ አይ ደለም። ይሁን እንጂ ቃለ አዋዲው ላይ ተመስርቶ እንደ ሀገሩ ሕግ አውጥቶ መተዳደር ግን ለቤተ ክርስ ቲያን ዕድገት የሚበጅ ነው በማለት የለንደን ደብረ ጽዮን ባለፈው ዓመት መተዳደሪያ ይሆናት ዘንድ የጸ ደቀውን ደንብ ለሌሎች ለተመሠረቱም ይሁን ለሚመሠረቱ ይጠቅማል በማለት እዚህ ላይ አውጥተናል።**

**ከዚህ በታች የተጠቀሱት ደግሞ ታቅደው ያልተፈጸሙ ነገር ግን ለሚቀጥለው ዓመት ለመሥራት የታቀዱ ናቸው፤**

1) **ለመናፍቃን መልስ ተብለው የቀረቡትን ወደ ውጭ ቋንቋዎች ማስተርጎምና ማቅረብ**

2) **ትምህርትና ወቅታዊ የቤተ ክርስቲያን ጉዳዮችን መወያያ ክፍል ማዘጋጀት ነው።**

**ከሞላ ጎደል የሠራነውና ልንሠራው ያቀድነው ይህ ሲሆን በዚህ ላይ ልትተባበሩና ወይም አስተያየት ያላ ችሁ ጻፉልን።**

**እግዚአብሔር አምላክ በዓሉን የሰላም፣ የደስታ እንዲያደርግልን፤ ለሀገራችን ኢትዮጵያ ሰላምንና በረከትን ፣ ለሕዝባችንም አንድነትንና ፍቅርን ይስጥልን።**

www.ethiopianorthodox.org team!

**ዌብ ማስተር**

**በእደ ማርያም እጅጉ ረታ**

**ግንቦት** 1999